ናንሲ ኤስ ግራዝሚክ ማርቲን ኦማሊ
የስቴቱ ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ አገረ ገዢ

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 W. Baltimore Street, Baltimore, MD 21201
www.marylandpublicschools.org

# የልዩ ትምህርት ፍትህ ሂደት አቤቱታዎችን በተመለከተ ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች የወላጅ መምሪያ

## 1. የፍትህ ሂደት አቤቱታ ምንድን ነው?

የፍትህ ሂደት አቤቱታ፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ጋር ሊያመራ የሚችል የአንድ አካላስንኩል የሆነ ወይም አለበት ተብሎ የሚጠረጠር ተማሪን መታወቂያ፣ ግምገማ፣ ትምህርታዊ ምደባ ወይም ተገቢ የነጻ የሕዝብ ትምህርት አቅርቦትን በተመለከተ ኦፊሲዬላዊ አቤቱታ ነው።

## 2. የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስገባት የሚችለው ማነው?

ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት[1] የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሊያስገባ ይችላል።

## 3. የፍትህ ሂደት አቤቱታ የማስገባው እንዴት ነው?

የፍትህ ሂደት አቤቱታዎን ከ *ግልግልና የፍትህ ሂድት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ* ፎርም ጋር አብሮ ማስገባት የተመረጠ ቢሆንም፣ ማንኛውም በጽሑፍ የቀረበ፣ የሚያስፈልገውን መረጃ ሁሉ አሟልቶ የያዘ ጥያቄ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሂደቱን ያስጀምራል። ፎርሙን ለማግኘት ለልጁ ትምህርት ኃላፊ የሆነው የሕዝብ ድርጅት ጋር፣ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ጋር (410-229-4281)፣ ወይም የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች (410-767-7770) ጋር መደወል ወይም መጻፍ ይቻላል። ፎርሙ የአስተዳደራዊ ቅሬታዎች ሰሚ ቢሮ ዌብሳይት www.oah.state.md.us እና የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ዌብሳይት ላይም www.marylandpublicschools.org ይገኛል (የDivision of Special Education/Early Intervention Services ገጽ ላይ ሂደው ከዛ የ Complaint Investigation and Due Process Branch ገጽን ይምረጡ)።

## 4. የፍትህ ሂደት አቤቱታዬን የምልከው የት ነው?

የፍትህ ሂድተ አቤቱታዎ ለተማሪው ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅት <u>እና</u> ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ መላክ አለበት። ፎርሙ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በእጅ ሊሰጥ ይችላል። የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ በኢሜል የተላኩ የፍትህ ሂደት

---

[1] እዚህ ሰነድ ውስጥ የሕዝብ ድርጅት የሚለው ስያሜ፣ ለአንድ ተማሪ የነጻ የሕዝብ ትምህርት አቅርቦት ኃላፊ የሆኑትን የትምህርት ሥርዓቶች ወይም ሌሎች የሕዝብ ድርጅቶችን አስመልክቶ ነው።

አቤቱታዎችን አይቀበልም፣ አድራሻው 11101 Gilroy Road, Unit E/Clerk's Office, Hunt Valley, MD 21031 ነው የፋክስ ቁጥሩም 410-229-4277 ነው። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የፍትህ ሂደት አቤቱታን ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ አስተላልፎ አይልክም።

5. የፍትህ ሂደት አቤቱታ ለማስገባት ያለው የጊዜ ገደብ ምን ያክል ነው?

ለአቤቱታው ምክንያት ስለሆነው ተከስቷል የተባለው ድርጊት ባወቁ ወይም አውቀው ከነበረበት ጊዜ በኋላ እስከ ሁለት (2) ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ይፍትህ ሂደት አቤቱታው መግባት ያለበት። ይህ የጊዜ ገደብ የማይመለከታቸው ጥቂት ልዩ ሁኔታዎች አሉ፣ በይበልጥ መረጃ ለማግኘት የሕዝብ ድርጅቱ የሰጥዎትን የሥርዓት መከላከያ ሰነድ ይመልከቱ።

6. የፍትህ ሂደት ችሎት ፊት የመቅረብ ዕድል ከመኖሩ በፊት አቤቱታውን ለመፍታት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

የፍትህ ሂደት ችሎት ዕድል ከመገኘቱ በፊት የ30 ቀን መፍትሔ ማግኛ ጊዜ አለ። ይህ ጊዜ እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ አለመግባባቱን ለመፍታት እንድትሞክሩ ይፈቅዳል። እርስዎ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ግልግልን ተጠቅሞ አለመግባባቱን ለመፍታት ሙከራ ለማድረግ ልትስማሙ ትችሉ ይሆናል፣ ካልሆነ ሁለቱም ወገኖች ስብሰባውን ለመተው ካልተስማሙ በስተቀር፣ የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ማግኛ ስብሰባ ለማድረግ ጊዜ ያስይዛል።

ስለ ግልግሉ ሂደት በይበልጥ መረጃ ለማግኘት የሥርዓት መከላከያ ሰነዱን ወይም የልዩ ትምህርት ግልግልን በተመለከተ ባብዛኛው የሚጠየቁ ጥያቄዎች የወላጅ መምሪያን ይመልከቱ።፡

7. የመፍትሔ ስብሰባ ምንድን ነው?

የመፍትሔ ስብሰባ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ አቤቱታውን ያስነሱትን ነገሮች ተነጋግራችሁ አለመግባባቱን ከተቻለ ለመፍታት ዕድል ይሰጣል።

8. የመፍትሔ ስብሰባ ጋር መሄድ የሚችለው ማነው?

እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ስብሰባው ላይ ማን ቢገኝ ተገቢ እንደሆነ ትወስናላችሁ። እርስዎ፣ ተገቢ የሆኑት የ IEP ቡድን አባሎች፣ እና ውሳኔ የማስተላለፍ ስልጣን ያለው የሕዝብ ድርጅቱ ተወካይ የመፍትሔ ስብሰባው ላይ መገኘት አለባችሁ። ሌሎች ተሳታፊዎች ልጅዎ፣ ደጋፊዎ ወይም ጠበቃዎ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ጠበቃዎ አብሮት ከመጣ የሕዝብ ድርጅቱም ጠበቃ መሳተፍ ይችላል።

9. የመፍትሔ ስብሰባ እንዲደረግ መጠየቅ አለብኝ?

የለብዎትም። ወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ካስገባ፣ ወገኖቹ የመፍትሔ ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ካልተስማሙ ወይም ወገኖቹ አለመግባባቱን በግልግል ለመፍታት ለመሞከር ካልተስማሙ በስተቀር፣ የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ስብሰባ ማዘጋጀት አለበት። የሕዝብ ድርጅቱ ከሆነ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን ያስገባው፣ የመፍትሔ ስብሰባ አስፈላጊ አይደለም። የሕዝብ ድርጅቱ አቤቱታ ሲያስገባ የመፍትሔ ስብሰባ አስፈላጊ ያልሆነው የሕዝብ ድርጅቱ አለመግባባቱን ለመፍታት ከዚህ በፊት ሞክሯል ተብሎ ስለሚገመት ነው።

10. **የመፍትሔ ስብሰባ የሚደረገው መቼ ነው?**

የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ስብሰባ እንዲያደርግ የሚጠበቅበት የፍትህ ሂደት አቤቱታው ከእርስዎ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ነው (አቤቱታው የአፋጣኝ ችሎት እንዲደረግ የሚያስፈልጉትን ነጥቦች ካላሟላ በስተቀር፣ ይህ ከሆነ ጥያቄ ቁጥር 13ን ይመልከቱ)። የሕዝብ ድርጅቱ አቤቱታዎ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባውን ካላደረገ ወይም ስብሰባው ላይ ካልተሳተፈ፣ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ቢሮ ጋር ደውለው የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳው በፍጥነት እንዲጀምር መጠየቅ ይችላሉ።

11. **የመፍትሔ ስብሰባ ላይ ሳልገኝ ብቀርስ?**

የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ ተገቢ ሙከራዎች አድርጎ ሳይገኙ ቢቀሩ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የአስተዳደር ሕግ ዳኛ አቤቱታዎን እንዲያስወግድ መጠየቅ ይችላል። አቤቱታው ከተወገደ ያንን አቤቱታ በተመለከተ የፍትህ ችሎት አይኪያሄድም።

12. **አለመግባባቱን ለመፍታት ለመሞከር ምን ያክል ጊዜ አለን?**

ባጠቃላይ እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ አለመግባባቱን ለመፍታት 30 ቀኖች አሏችሁ። ሆኖም እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ መሻሻል አለ ብላችሁ ከተስማማችሁና ጊዜውን ማራዘም ከፈለጋችሁ፣ ይህንን ማድረግ የተፈቀደ ነው። የተፋጠነ ችሎት መደረግ ያለበት ጉዳዮች ላይ፣ እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ አለመግባባቱን ለመፍታት ለመሞከር 7 ቀኖች አሏችሁ።

13. **የመፍትሔ ስብሰባው ላይ ስምምነት ላይ ሳንደርስ ብንቀር ምን ይሆናል?**

እርስዎና የሕዝብ ድርጅቱ ስምምነት ላይ ካልደረሳችሁ፣ የመፍትሔ ማግኛ የጊዜ ገደቡን አራዝማችሁ ስብሰባ ማድረግ እየቀጠላችሁ አጥጋቢ መፍትሔ እስከምታገኙ ድረስ መቀጠል ትችላላችሁ። ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ አለመግባባቱን በግልግል ለመፍታት መመከር ትችላላችሁ፣ ወይም የፍትህ ችሎት ለማድረግ መቀጠል ትችላላችሁ።

14. **የፍትህ ሂደት ችሎት ላይ ምን ይሆናል?**

የፍትህ ሂደት ችሎት የሚኪያሄደው ከአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ በሚመጣ የአስተዳደር ሕግ ዳኛ መሪነት ሲሆን፣ ከሁለቱም ወገኖች ማስረጃ ወስዶ ስለ አለመግባባቱ ውሳኔ ይሰጣል። ስለ ፍትህ ሂደቱ ሥርዓቶችና መብቶች ልዩ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሥርዓት መከላከያ ሰነዱን ይመልከቱ።

15. **ጠበቃ ያስፈልገኛል?**

አያስፈልግዎትም፣ ሆኖም የሂደቶቹ ጸባይ ሕግ-ነክ በመሆኑ ምክንያት ብዙውን ጊዜ ወላጆች በአማካሪ/ጠበቃ ተወክለው የሚቀርቡ ሲሆን፣ ችሎት ሂደው እራሳቸውን ወክለው መቅረብም ይችላሉ።

በነጻ ወይም በቅናሽ ዋጋ ሕግ-ነክ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡ የድርጅቶች ስም ዝርዝር ለማግኘት የ*ግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ* ፎርምን ይመልከቱ፡ ወይም የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ዌብ ሳይትን በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ ይጎብኙ (በመጀመሪያ Divisions, Special Education Early Intervention ን መርጠው ከዚያ Complaint Investigation and Due Process Branch የሚለውን ይምረጡ)።

16. የፍትህ ሂደት የጊዜ ገደብ ምን ያክል ነው?

የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ (የመፍትሔ የጊዜ ገደብ) ለእርስዎ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መፍትሔ ካላገኘ የፍትህ ችሎቱ ሊደረግ ይችላል። የአስተዳደር ሕግ ዳኛው ከዛ ቀጥሎ ችሎቱን ለመምራትና የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት 45 ቀናት አለው። እርስዎ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ጥያቄ ባቀረባችሁ ጊዜ፣ የውሳኔ ማስተላለፊያ የጊዜ ገደቡ መራዘም ይችላል።

17. የተፋጠነ ችሎት ለማግኘት ምን መሟላት አለበት፣ የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳስ እንዴት ለውጥ ይኖረዋል?

ልጅዎ በወቅቱ ፍቃድ የተሰጠው የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ ተመዝግቦ እና እየሄደ ካልሆነ፣ ወይም አለመግባባቱ የገለጻ ውሳኔን በተመለከተ ከሆነ፣ ወይም ቅጣት ባስከተሉ ባሕርዮች ምክንያት የሚደረግ የምደባ ለውጥን በተመለከተ ከሆነ፣ ችሎቱ በተፋጠነ መንገድ መደረግ አለበት። በነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ጊዜ የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ 7 ቀናት ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባ ማድረግ አለበት፣ ችሎቱ አቤቱታው በደረሰ በ20 የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ መደረግ አለበት፣ እንዲሁም ችሎቱ በተፈጸመ በ10 የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔው መሰጠት አለበት።

18. ከችሎት በፊት የሚደረግ ስብሰባ ምንድነው?

ችሎቱ ስንት ቀን እንደሚያስፈልገው ለመወሰን እንዲቻል፣ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ስለ አለመግባባቱ በዝርዝር ለማወቅ በስልክ የሚደረግ ቅድመ-ችሎት ስብሰባ ይመራል። እርስዎና ምስክሮችዎ ችሎቱ ላይ መቼ መገኘት እንደምትችሉ ለመወያየት፣ እዚህ ስብሰባ ላይ ተዘጋጅተው መቅረብ አለብዎት።

19. ያስገባሁትን የፍትህ ሂደት አቤቱታ መልሼ ማውጣት ብፈልግስ?

አቤቱታዎን መልሰው ማውጣት እንደሚፈልጉ የሚገልጽ የተፈረመ ደብዳቤ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በእጅ ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ እና ለሕዝብ ድርጅቱ በተቻለ

መጠን በቶሎ መስጠት አለብዎት። ደብዳቤው አቤቱታውን ለምን መልሰው እንደሚያወጡ የሚያስረዳ መረጃ መያዝ ይችላል።

20. ጥያቄዎቼን በሙሉ አልመለሳችሁም። እርዳታ ለማግኘት የት መሄድ እችላለሁ?

በመጀመሪያ የሕዝብ ድርጅቱ የሰጥዎትን የሥርዓት መከላከያ ሰነድ ያንብቡ። ለሌሎች ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚችሉት ለልጁ ትምህርት ኃላፊ ከሆነው የሕዝብ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ተገቢ ሠራተኞች፣ ለመሳካት አጋሮች ወይም የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች ማዕከል (Partners for Success or Family Support Services Center)፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮ (410-767-0267 ወይም 1-800-535-0182, ext. 0267)፣ ወይም የአስተዳደራዊ ቅሬት ሰሚ ቢሮ ሠራተኛ ቢሮ (410-229-4281)። የልዩ ትምህርት ጉዳዮችን በተመለከተ በነጻ ወይም በአነስተኛ ክፍያ እርዳታ የሚሰጡትን ድርጅቶችንም ማማከር ይችላሉ (የነዚህ ድርጅቶች ዝርዝር የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም ላይ ተያይዞ ይገኛል)።

*የገንዘብ ድጋፍ የቀረበው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ከ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A070035A፣ የዩ ኤስ የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ በኩል ነው። በዚህ ውስጥ የተገለጹ አስተያየቶች የዩ ኤስ የትምህርት ክፍልን ወይም ማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን ወክለው አይደለም እንደሱም መታየት የለባቸውም። የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከልዩ ትምህርት መርሀ ግብሮች ቢሮ፣ ከልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮና ከዩ ኤስ የትምህርት ክፍል ነው። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ።*

*የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጸዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር (410)767-0433 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር (410)767-0431 መገናኘት ይችላሉ። የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶችን ክፍል በስልክ ቁጥር (410)767-0858 ወይም በፋክስ (410)333-1571 ይገናኙ።*

Dev. 10/2007